# BAG it RIGHT

## በፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ

PRINCE GEORGE'S COUNTY MARYLAND

Angela D. Alsobrooks
*County Executive*

**እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1** ፣ 2024 ጀምሮ የችርቻሮ መደብር የእቃ መያዢያ የፕላስቲክ ከረጢት ለሸማቾች እንዳያቀርብ የፕሪንስ ጆርጅ ካውንቲ እገዳ ጥሏል፣ ነገር ግን፣ ይህ ክልከላ ተግባራዊ የማይደረግባቸው የተወሰኑ ሁኔታዎች አሉ*፣ በምትኩ ለደንበኛው ለሚቀርብ ለእያንዳንዱ የወረቀት የእቃ መያዢያ ከረጢት ወይም ድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውል ለሚችል ቦርሳ ቢያንስ 10 ሳንቲም ማስከፈል እና መያዝ አለበት።

### እገዳው ለምን ተጣለ?

አካባቢን/ስነ-ምህዳርን፣ የባህር ውስጥ ህይወትን ከጉዳት ለመጠበቅ እንዲሁም ቆሻሻን ለመቀነስ።

### እገዳው ማንን ይመለከታል?

ሁሉም የችርቻሮ መደብሮች፣ ሬስቶራንቶች፣ የግሮሰሪ መደብሮች፣ ወይም በሚሸጠው ምርት ወይም አገልግሎት ምክንያት ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚል የፕላስቲክ ከረጢት ለደምበኞቹ የሚሰጥ ሌላ ማንኛውም ለትርፍ የተቋቋመም ይሁን ለትርፍ ያልተቋቋመ ተቋም።

# የዕቃ መያዢያ ከረጢት ክፍያ መመሪያ




## ምን ይፈቀዳል

**መደብሮች እና ሬስቶራንቶች የወረቀት ከረጢቶችን ወይም እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ከረጢቶችን ለመጠቀም/ለመሸጥ ቢያንስ 10 ሳንቲም ማስከፈል አለባቸው።**

"እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል የዕቃ መያዢያ ከረጢት" ማለት በልዩ ሁኔታ የተነደፈ እና በተደ ጋጋሚ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል እንዲሁም ስፌት እጀታ ያለው ቦርሳ/ከረጢት ማለት ሲሆን፤ ከመደ በኛ ጨርቅ ወይም ሊታጠብ ከሚችል ጨርቅ የሚሰራ ወይም ከፕላስቲክ ያልተሰራ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የሚውል ዘላቂ/የሚበረክት ቁስ ማለት ነው።

## እገዳው የማይመለከታቸው

**ለሚከተሉት ዓላማዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ የፕላስቲክ ከረጢቶች፡-** ፍራፍሬ፣ አትክልት፣ ለውዝ፣ እህል፣ ከረሜላ ወይም አነስተኛ የሃርድዌር ንጥሎችን ጨምሮ የጅምላ እቃዎችን ለመጠቅለል የሚያገለግሉ፤ የታሸጉም ሆኑ ያልታሸጉ፣ ቀዝቃዛ ምግቦች፣ ስጋ ወይም አሳን ለመጠቅለል የሚያገለግሉ፤ አበባዎችን፣ በማሰሮ ውስጥ የበቀሉ እፅዋቶችን ወይም ሌሎች እርጥብ ነገሮችን ለመጠቅለል የሚያገለግሉ፤ ያልታ ሸጉ ምግቦችን ወይም የዳቦ ምርቶችን ለመያዝ የሚያገለግሉ፤ ጨርቃጨርቆችን ወይም ደረቅ-የታጠቡ ልብሶችን ለመያዝ ወይም ለመጠበቅ የሚያገለግሉ፤ ሙሉ ልብሶችን፣ ቀሚሶችን እና መደበኛ አልባሳትን ለመያዝ/ለመከላከል የሚያገለግሉ፤ በህይወት ያለ ዓሳን፣ ነፍሳትን፣ ሞለስከሶችን ወይም ክረስታሺያንስን ከችርቻሮ መደብር ለመውሰጃ የሚያገለግሉ የፕላስቲክ ከረጢቶችን እገዳው አይመለከትም።

**ሚከተሉት አገልግሎቶች ላይ ለሚውሉ የወረቀት ከረጢቶች የሚከፈል ክፍያ፤** ከፋርማሲ የተገዙ መድ ኃኒቶችን ለመያዝ፤ በመኪና ውስጥ ሆነው እየነዱ በመስኮት በሚሰጥ መስተንግዶ (drive-through) ለሚቀርብ የተዘጋጀ ምግብ መጠቅለያ፤ እንዲሁም ሙሉ አገልግሎት በሚሰጥ ሬስቱራንት ውስጥ ከተመ ገቡ በኃላ ለተረፈ/ትርፍራፊ ምግብ መያዣ የሚሰጡ የወረቀት ቀረጢቶችን እገዳው አይመለከትም።

**የታገደው ምንድን ነው?**
**ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ የፕላስቲክ ከረጢቶች**



**አሁን ያቅዱ። ለሸመታ ሲወጡ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ከረጢት ማምጣት ይጀምሩ!**

ለበለጠ መረጃ **mypgc.us/bagitright** ን ይጎብኙ